ህዳር 2002 ዓ.ም.

# የአሮብ አናሳ ብሄረሰብ ህልወና ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ማዕረታዊ ችግሮችና ማስኤዎቻቸው

## ከበየነ ገብራይ ፤

### መግቢያ

ይህን መጣጥፍ እንድጽፍና ለወይይት እንዳቀርብ ያነሳሳኝ የአሮብ አናሳ ብሄረሰብ ለብዙ ዓመታት ይዞት የቆየው ሜሬቱ ለሁለት ተከፍሎ፣ ባህሉ፣ ቋንቋወና ታሪኩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ እየሄደ ያላለበት ሁኔታ ወስጥ እየገባን ነው የሚል እምነት ስላደረብኝ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በርካታ የብሄረሰቡ አባላት በተለይ ደግሞ ወጣቱ ትወልድ በተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት አከባቢወን እየለቀቀ በመፍለስ ላይ ስለሆነ ነው። ሁኔታው አሁን እንዳለው እኔ ምንአገባኝ፣ ይህን ብል ምን እባል ይሆን በሚል ፍረሃት በዝምታ ከቀጠለ አሮብ የሚባል አናሳ ብሄረሰብ ነበር ወደሚል ታሪክነት ሊቀየር ይችላል የሚል ስጋትም ስላደረብኝ ስጋቴን ከወንድሞቼና እህቶቼ ጋር በማጋራት፣ ለመፍትሄ ፍለጋ በጋራ ልንሰራ የምንችልበት ሁኔታ ለማመቻቸት ለምናደርገው ወይይት እንደ መነሻ ይረዳ እንደሆነ በሚል ነው።

በዚህ መጣጥፍ የማቀርባቸው ሃሳቦች፣ ሚጃዎችና ትችቶች ከፖሊቲካ አመለካከቴ ጋር ምንም ግኑኝነት የሌላቸው፣ በኔ እይታ የአሮብ አናሳ በሄረሰብ ዛሬ የሚገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ብቻ የተመሰረቱ ናቸው። ስለሆነም የማቀርባቸው ሚጃዎች፣ ሃሳቦችና ትችቶች የተሳሳቱ ናቸው የሚል/የምትል ካለ/ች ይህ ለወይይት ማንደርደሪያነት ተብሎ የቀረበ መሆኑ በሚዳት በንጹህ ህሊና መጣጥፌን እንድተቸው፣ እንዲያዳብረው አሳስባለሁ።

በዛሬው የመጀመሪያ መጣጥፌ በዋናነት የአሮብ አናሳ ብሄረሰብ ህልወናን አደጋ ወስጥ እያስገቡ ያሉ በምላቸው ችግሮችና ማንስኤዎቻቸው ላይ ብቻ ለማተኮር ሞክሬያለሁ። ችግሮቹን ለመፍታት ምን መደረግ አለበት የሚለውን የራሱን ርእስ ይዞ ለወደፊት በሌላ መጣጥፍ ለማቅረብ በይደር አሳድሬዋለሁ። ይህ እንዲሆን የፈለግኩበት ምክንያት ደግሞ በመጀመሪያ ሁላችን ችግሮቹንና ማንስኤያቸውን በግልጽ ለይተን ብናስቀምጣቸው ለጋራ መፍትሄ ፍለጋ ያመቻናል፣ ይቀለናልም የሚል እምነት ሳላለኝ ነው።

## የአሮብ አናሳ ብሄረሰብ ዛሬ ያለበት ተጨባጭ ሁኔታው ምን ይመስላል?

ብሄረሰባችን ዛሬ በተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት እንደ አንድ አናሳ ብሄረሰብ የመቀጠል ዕድሉ አደጋ ወስጥ ገብቷል በሚለው ብዙዎቹ የብሄረሰቡ ተወላጆች እንደሚስማሙ ጥርጥር የለወም። ብዙ ወደ ሩቅ ሳይከድ በቅርብ ዓመታት ብቻ በአከባቢው የተከሰተው ድርቅና የተፈጸሙ ድርጊቶችን በማስቀመጥ ይህን ሃቅ ለማሳየት ይቻላል። ዋና ዋና የቅረብ ጊዜ የብሄረሰቡን ህልወና በቀጥታ ከሚነኩ ድርጊቶች ማሳራዊ ናቸው የምላቸውን ለመጥቀስ ያህል፣ ለብዙ ዓመታት የቀጠለው ድርቅ ዛሬም አከባቢወን እንዳጠቃ ነው፣ ዛሬ የአሮብ ሜሬት ለሁለት ተከፍሏል። ቋንቋችን፣ ባህላችን፣ ታሪካችን ከቀን ወደ ቀን እየተሸረሸረ ነው። በርካታ የብሄረሰቡ አባላት አከባቢወን እየለቀቁ ወደተለያየ አቅጣጫ እየፈለሱ ነው። ይህ ክስተት በንጹህ ህሊና የህዝባችንና የአከባቢያችን ወቅታዊ ሁኔታ የሚመለከትና የሚከታተል ወገን ሁሉ ሊያየው የምችል ያፈጠጠ፣ ያገጠጠ ሃቅ ነው። ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ግን ይህን ያፈጠጠ ሀቅ ለማየት የማይፈልጉ የተወሰኑ የአገዛዙ አባላትና ደጋፊ የሆኑ የብሄረሰቡ ተወላጆች መኖራቸወም የሚታወቅ ነው። አሁን ስልጣን ላይ ያለው አገዛዝም እነዚህና ሌሎች ማሰረታዊ የሆኑ በቀጥታ በአገዛዙ ካድሬዎችና አስተዳዳሪዎች የሚፈጸሙ ችግሮች እንዲታወቁና በይፋ እንዲወጡ አይፈልግም። ግልጽ ወይይት በሁሉም ጉዳዩ የሚመለከተን ወገኖች በችግሮቹ ዙሪያ እንዲደረግ አይፈልግም። ስለሆነም የኸው እስከዛሬ ዝምታ ነግሶ የአሮብ አናሳ በሄረሰብ ችግር ከቀን ወደ ቀን እየባሰበት እየቀጠለ ነው።

ይህ ዝምታና ሚፈራራት ማሰበር የነበረበት ድሮ ቢሆንም አሁንም ምንም ካለማድረግ ዘግይቶም ቢሆን መጀመር ይሻላልና ወይይቱን፣ መፍትሄ ፍለጋወን እንጀምረው። ስለ አሮብ አናሳ ብሄረሰብ ህልወናና እድገት ሁላችን የብሄረሰቡ ተወላጆች እኩል ሃላፊነትና ግዴታ እንዳለብን ተገነዝበን ለችግሮቹ መፍትሄ ፍለጋ አብረን እንስራ ባይ ነኝ። ስለሆነም ስለብሄረሰባችን ሁኔታ ግልጽ ወይይትና የጋራ መፍትሄ ፍለጋ ለምናደርገው ወይይት እንዲረዳ እነሆ እኔ የአሮብ አናሳ ብሄረሰብ ህልወና አደጋ ወስጥ ያስገቡ ናቸው የምላቸው ማሰረታዊ ችግሮችና ማንስኤዎቻቸው እንደምከተለው አቀርባለሁ።

## የአሮብ አናሳ ብሄረሰብ ህልወናን አደጋ ወስጥ ያስገቡ ማስረታ ችግሮች የተኞቹ ናቸው?

1. አከባቢው በሞቃርጥ ድርቅ መመታትና ወደ ምድረበዳነት መቀየር
2. የወረዳው ዋና ከተማ ከታሪከቷ ዓሊተና ወደ ዳወሃን በግድ መቀየር
3. የወጣዮች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እየተጠቀሙ አከባቢወን ለቀው ለመጥፋት መፈለግ
4. ለማመን አሰቸጋሪ የሆነ የባህልና እምነት ዝቀጠት ማከሰት
5. ሽማግሌዎች አከባቢወን እየለቀቁ ወደ ትልልቅ ከተሞች መፍለስ
6. የሻዕቢያ ወረራ፣ ያስከተለው የህይወት፣ የንብረት ወድመትና የተወሰነ መሬት ለኤርትራ ማስጠት
7. በአከባቢው ድንበር ጥበቃ በሚል የሰፈረው ሰራዊት እያስከተለ ያለው የትዳርና ኑሮ መፋለስ
8. መደምደሚያ

## 1. አከባቢው በሞቃረጥ ድርቅ መመታትና ወደ ምድረበዳነት መቀየር

በአሮብ እኔ ገና ትንሽ ልጅ እያለሁ አብዛኛው አከባቢ በጫካ የተሸፈነ ነበር። ይህ በመሆኑም በየዓመቱ ወቅቱን ጠብቆ የሚመጣው የበልግም ሆነ የክረምት ዝናም ምንም ሳይዛነፍ ወቅቱን ጠብቆ ይዘንብ ነበር። በመሆኑም ህዝቡ ምንም ዓይንት የሚባላ እህል ሆነ የሚጠጣ ወሃ የማጣት ችግር የሚባል ነገር አያወቅም ነበር። ይለቁንስ ከአሮብ አከባቢ የሚመሚተው ማርና ቅቤ በሌላው አከባቢ ከሚሚተው ጋር ሲነጻጸር በጥራቱም ሆነ በብዛት የላቀ ነበር።

ትንሽ ከፍ ብዬ ወደ 20 ዓመት ዕድሜ አከባቢ ስደርስ በየመንደሩ ተጨማሪ የእርሻ መሬት ፈላጊ አርሶ አደር ወጣቶች እየተበራከቱ ማጡ፡ እነዚህ አዳዲስ የእርሻ መሬት ፈላጊ ወጣት አርሶ አደሮች የእርሻ መሬትን ለማግኘት በሚል በየአከባቢው የነበረው ጫካን በከፍተኛ ደረጃ መመንጠር ጀመሩ። ጫከው እየተመነጠረ ሲሄድ ደግሞ ወቅቱን ጠብቆ የሚጥል የነበረው ተፈጥሮአዊ ዝናምም ቀስ በቀስ እየቀነሰ መጣ፡ ዛሬ ደግሞ በአሮብ ዛፎች እንዳሉ ወድመው መሬቱ እርቃኑን የቀረበት፣ ህዝቡም እንዳለ የውጭ ምጽዋት ተመልካች/ጠባቂ እንዲሆን የሆነበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን።

የድርቁ አጀማመርና ዕድገት ከላይ ባጭሩ እንዳስቀመጥኩት ሆኖ፣ ለድርቁ ዋና መንስኤ የሆነው ይህን የጫከው ምንጠራ ለማስቀረትና ለአዲሶቹ አርሶአደሮች የእርሻ መሬት ከጫከው ምንጠራ ውጭ ሊያገኙ የምችሉበት መንገድ መፈለግ ባለፉት ሆነ አሁን ስልጣን ላይ ባለው አገዛዝ ሲፈለግ እየተማለከትን አይደለንም፡ ይባስ ብሎ ባሁኑ ጊዜ ከኢትዮ ኤሪትርያ ጦርነት በኋላ ድንበርን ለማጠበቅ በአከባቢው የሰፈረው ሰራዊት ለምግብ ማበሰያ የሚያስፈልገወን ማገዶ ፍለጋ አንዳንድ ቀርተው የነበሩ ዛፎች ምንጥራ ላይ ከህዝቡ ጋር ተጨምሮበት ዛፎቹ ተቆርጠው ስላለቁ ስሮችንም ሁሉ ቆፍሮ ለማገዶ ምንጠራ ብሶበት እየቀጠለ ነው።

ዛሬ መሬቱ እርቃኑ በቀረበት፣ ካለው የህዝብ ብዛት አኳያ አሁን ማግኘት የምችሉት የበሬ ግንባር የሚያክል መሬት ብቻ በሆነበት ሁኔታ ወጣት ገበሬዎች በቀያቸው የተለመደወን ኋላ ቀር የግብርና መሳሪያና ዘዴ እየተጠቀሙ ወቅቱን ጠብቆ የሚመጣወን ዝናም ብቻ እየጠበቁ አርሶ አደሮች በአሮብ ወረዳ ኑሮአቸወን በእርሻ ሊገፉ የምችሉበት ሁኔታ እየተሟጠጠ መጥቷል። ስለሆነም ከሜሬቱ ከርሰምድር ሊገኝ የምችለወን ወሃ ተጠቅሞ፡ በጣም ኋላቀር የሆነወን የእርሻ ዘዴ ቀይሮ ህዝቡ ራሱን ችሎ በአከባቢው እንዲኖር ለማድረግ ካልተቻለ ወጣት ገበሬዎች አከባቢወን እየለቀቁ ማስደድ ይቀጥላል።

## 2. የወረዳው ዋና ከተማ ከታሪካዊቷ ዓሊተና ወደ ዳወሃን በግድ መቀየር፣

አሁን ስልጣን ላይ ያለው የኢህአዴግ አገዛዝ የፋስሽታዊ ደርግን አገዛዝ በጠመንጃ ሃይል ገርስሶ ስልጣን በ1983 ግንቦት በኢትዮጵያ ስይዝና በአሮብ የመጀመሪያ የአከባቢው አስተዳደር በቁጥጥሩ ስር ሲማስርት ከሁሉ አሰቀድሞ ያደረገው ነገር ቢኖር የአሮብ ወረዳ ዋና ከተማ ከዓሊተና ወደ ዳወሃን መቀየር ነው። ዓሊተና ከአሮብ ህዝብ ጋር ያላት ታሪካዊ ግኑኝነትና የምንነት ተምሳሌነት ሁላችን በሚገባ የምናወቀው ነው። ዓሊተና እንደ 3ቱ አሮብ ማእከላዊ መናኛ በመሆን ለብዙ ዘመን አገልግላለች። ከዚህ በተጨማሪም ከኢህአዴግ በፊት በነበሩ አገዛዞች ዘመንም የወረዳው ዋና ከተማ ሁና ቆይታለች። ከብዙ ዘመናት በኋላ የዓሊተና የወረዳው ዋና ከተማ መሆን ተሰርዞ ወደ ዳወሃን የተቀየረው አሁን በኢህአዴግ የአገዛዝ ዘመን ነው። ይህ የወረዳው ዋና ከተማነት ከዓሊተና ወደ ዳወሃን መቀየር የአሮብ ህዝብ ይሁኔታም ተጨምሮበት እንደሆነ በርግጠኝነት ለመናገር ባልችልም የአሮብ ህዝብ እልል ብሌ የተቀበለው ወሳኔ ነው ብዬ ግን አላምንም፡

እኔ ከዘመናዊ የከተሞች ዕድገት ጋር በተያያዘ የአሮብ ወረዳ ዋና ከተማ ከዓሊተና ወደ ሌላ ለዘመናዊ ከተማ ግንባታ አመች ወደሆነ ቦታ መቀየርና ማንባት ጋር ችግር የለብኝም። የአሮብ ወረዳ ዋና ከተማ ከዓሊተና ውጭ በፍጹም መቀየር የለበትም የሚል ጭፍን እምነትና አመለካከትም የለኝም። ግን ዓሊተናና ዳውሃን ለከተማነት ያላቸውን ተፈጥሮአዊ አቀማመጥና ለአንድ ዘመናዊ ከተማ ዕድገትና ስፋት ያላቸውን የቦታ አቀማመጥ ስመለከት ዳውሃን ከዓሊተና የተሻለ ለዘመናዊ ከተማ ግንባታ አመችነት የተመረጠችበት ምክንያት ፈጽሞ አይገባኝም። ስለሆነም የአሮብ ወረዳ ዋና ከተማነት ከዓሊተና ወደ ዳውሃን የተቀየረው በአገዛዙ ፍላጎትና ዕቅድ ብቻ እንጂ በህዝቡ ፍላጎት አይደለም በሚለው በጽኑ አምናለሁ። አገዛዙ ይህን ያደረገበት ማሰረታዊ ምክንያት ደግሞ አገዛዙ ዓሊተና ከህዝቡ ታሪክና ምንነት ጋር ያላት ከፍተኛ ትስስር በሚገባ ስለሚያውቅ ህዝቡን ከዚህ ታሪካዊና የምንነት ትስስሩ ለማላቀቅ ሆን ተብሎ የተደረገ ድርጊት ነው ባይ ነኝ። ይህ ትክክል አይደለም ብሎ የሚከራከር ካለ/ች በማስረጃዎች አስደግፌ ጭብጤን ለማቅረብ ስለምችል ይህን በሚቀጥለው መፍትሄ ፍለጋ ላይ በምናደርገው ወይይት በስፋት እመለስበታለሁ።

## 3.የወጣቶች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እየተጠቀሙ አከባቢውን ለቀው ለመጥፋት መፈለግ

በ1983 ዓ.ም. ወታደራዊው የደርግ አገዛዝ ተገርስሶ ኢህአዴግ በትረስልጣኑን በኢትዮጵያ እንደያዘ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ሰፍኗል፣ የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ተረጋግጧል፣ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች በሂደት ይወገዳሉ ተብሎ ብዙ ቢሰበክም የአሮብ ህዝብ በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ የወጣቱ ትወልድ ችግሮች የሚቀርፍ ሁኔታ በአከባቢው አልተፈጠረም። ስለሆነም የአሮብ ህዝብ በተለይ ደግሞ ወጣቱ በደርግ ፋሽስታዊ አገዛዝ ዘመን የጀመረው ማስደድ አሁንም አላቆመም። የወጣቱ ስደት በፋሽታዊ የደርግ አገዛዝ ዘመን ከነበረው በባሰና በሰፋ ሁኔታ እየቀጠለ ያለበት ሁኔታ ላይ ነው ዛሬም የምንገኘው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ወጣቶችን በተደራጀ መልክ እያሰባሰቡ ወደ እስራኤል በገንዘብ የማጓጓዝ አዲስ ስደት ተጀምሯል። የተወሰኑ ወጣቶችና ህጻናትም ቀያቸውንና ወላጆቻቸውን በመተው ወደ ኤርትሪያ በመሄድ የኢህአዴግ አገዛዝን በጠመንጃ ሃይል እናሰወግዳለን ከሚሉ በሻዕቢያ ከሚታገዙ ሃይሎች ጋር እየተቀላቀሉ ነው ያሉት።

ስለ ወጣቶች አሁንም እየተሰደዱ መሆናቸውን ሁላችን የብሄረሰቡ ተወላጆች የምንሰማማበት ጉዳይ ሆኖ፣ ለወጣቶቹ የስደት ማንስኤ ምክንያት ላይ ግን አንዳንዶቻችን በጣም እንለያያለን። አንዳንድ በዲያስፖራ የሚኖሩ የአገዛዙ ደጋፊ ነን የሚሉ የብሄረሰቡ ተወላጆች አቶ ሓጎስ ዮሃንስና አቶ አብራሃ ስብሓትን በመሳሪያነት በማጠቀም ለአሮብ ወጣቶች ወደ ተለያየ አቅጣጫ ፍልሰት ማሰረታዊ ምክንያት ራሱን IRAA በሚል የሚጠራ ቡድን የሚያደርገው ቅስቃሳና ፕሮፓጋንዳ ነው በሚል በግልጽ በጽሁፍ አሰቀምጠዋል። ለነዚህ ወገኖች ያለኝ መልስ ባጭሩ አህያውን ፈርቶ ዳወላውን የሚል ሆኖ፣ እኔ ለአሮብ ወጣቶች ወደ ሻዕቢያ መኮብለል ሆነ ወደ ተለያዩ አቅጣጫ ማሰደድ፣ ገፊና ቀስቃሽ ሃይል IRAA የተባለው ቡድን ሳይሆን አሁን ስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ነው እላለሁ። እናንተስ የተወደዳችሁና የተከበራችሁ ሞላው የአሮብ ብሄረሰብ አባላት ለአሮብ ወጣቶች እንደዚህ ወደተለያያ አቅጣጫ ፍልሰት ትክክለኛ ምክንያት/ቶች ወይም ማንስኤ ምንና ማን ነው ትላላችሁ?

ለወጣቶቹ ፍልሰት ማሰረታዊ ምክንያት አሁን ስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ነው ለምን እንደምል ምክንያቶቼንና የመፍትሄ ሃሳቦቼን በቀጣዩ መፍትሄዎች ፍለጋ በምናደርገው ወይይታችን በስፋት እመለስበታለሁ።

እንደኔ እምነትና ግንዛቤ የአሮብ ወጣቶች ዛሬ ገብተወበት ያለው የህልወናና የምንነት ወኻንብር ማን ያምጣው ማን በሚይቸግር በቀላሉ ለፈታ ወደሚይችልበት ወስብስ ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህ ዓይንት ወስብስብና ጥልቅ ችግር ደግሞ የሁሉም ዜጋና የባለሞያዎች ከፍተኛ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው። እንደ አናሳ ብሄረሰብ ለዚህ ችግር መፍትሄ ባስቸኳይ በአንድነት ካልፈለግንለትና ካላገኘንለት በአከባቢው አሁን ቀርተው ያሉት ወጣቶቹም ቢሆኑ አጋጣሚውን ካገኙ አከባቢውን ለቀው ለማሰደድ እንጂ በአከባቢው ለመኖር ፍላጎት እንደሌላቸው ሁኔታውን በቅርበት የሚከታተሉ ወገኖች የሚያረጋግጡት ሃቅ ነው። ስለሆነም ይህ ችግር ከሁሉም የብሄረሰቡ ችግሮች ይበልጥ ቱክረት ሊሰጠውና አስቸኳይ መፍትሄም ሊፈለግለት የሚገባ አንገብጋቢ ከሚባሉ ችግሮቻችን ግንባር ቀደሙ ነው።

## 4.ለማማ አስቸጋሪ የሆነ የባህልና የእምነት ዝቅጠት መከሰት

በኔ የወጣትነት ዕድሜ ወቅት አንድ የአሮብ ብሄረሰብ አባል ከትዳሩ ውጭ የግብረ ስጋ ግኑኝነት ቢያደርግ/ብታደርግ እንደ ትልቅ ጥፋት/ሃጢአት ይታይ ነበር። ልጅ ቢወልድ/ብትወልድ ደግሞ በጣም ትልቅ ነውር ነበር። በመሆኑም ከትዳር ውጭ የግብረስጋ ግኑኝነቶች በጣም ወሱንና የሚጸየፍም ተግባር ነበር። አንዳንድ አልፎ አልፎ ከትዳር ውጭ የሚወልዱ

የብሄረሰቡ አባላት ሲገኙም ባደረጉት ጥፋት በእምነታቸው መሰረት ህዝብ በተሰበሰበት ቦታ በግልጽ ፊት ለፊት ወጥተው አጥፍቻለሁና ይቅርታ ይደረግልኝ በማለት ህዝቡን ይቅታ ይጠይቁ ነበር።

ዛሬ ግን በርካታ ወጣቶች ከትዳር ውጭ ሲጋሩ፣ ያለ ዕድሜያቸው ሁሉ ሲወልዱ፣ በጣም ቅርብ የሆኑ የስጋ ዘመዶችም ሲጋሩና ሲዋለዱም እየተማለከትን ነው። በተጨማሪም አሁን በአከባቢው በተስፋፋው ቅጥ ያጣ የግብረስጋ ግኑኝት ምክንያትም በርካታ ወጣቶች የኤድስ በሽተኛ እየሆኑ ነው፣ በርካታዎቹም ህይወታቸውን እያጡ ነው።

ሌላም ባሁኑ ጊዜ በተለያዩ የአርብ ወረዳ በትናንሽ መንደሮች ሁሉ ማጠጥ እንደ ባህል በማሻጥ ላይ ነው። በተለይ እንደ ዳወሃንና ዓሊተና በመሳሰሉ ከተሞች ደግሞ ወጣቶቹ በማጠጥ ሃይል ተገፋፍተው እርስ በርስ ሲጣሉና ሲፈናከቱ የሚውሉበት ሁኔታ እየታየ ነው።

<u>ይህ ሁሉ በብሄረሰቡ ባህልና እምነት ያልነበሩ አዲስ የባህልና የእምነት ዝቅጠቶች ለምን ባሁኑ ወቅት እየተከሰቱ ናቸው? ይህ የወጣቶቹ የባህልና እምነት ዝቅጠት ምን ያመላክታል? ሁኔታው እንደዚህ ከቀጠለ ለወደፊቱ ምን ዓይንት ወጣትና ህብረተሰብ ሊኖረን ይችላል? ለዚህ የወጣቶቹ የባህል ዝቅጠትና የምንነት 'ክራይሲስ' በትክክል ምክንያቱ ምንድን ነው? ለወጣቶቹ በዚህ ክራይሲስ ወስጥ መግባት በትክክል ተጠያቂው ማን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች በሁላችን ባለጉዳዮቹ ሜልስ የሚያስፈልጉዋቸው ማስረታዊ ጥያቄዎች ናቸው።</u> ስለሆነም ራሱን በቻለ መጣጥፍ ለወደፊት በስፋት የምማለስበት ይሆናል።

## 5. <u>ሽማግሌዎች አከባቢውን እየለቀቁ ወደ ከተሞች መፍለስ</u>

በደርግ አገዛዝ ዘመን የተጀሚወና አሁን በኢህአዴግ አገዛዝ ዘመንም በከፍተኛ ቁጥር የቀጠለው በውጭ ሆነ በከተሞች ልጅ ወይም ዘመድ ያላቸው ሽማግሌዎችና አንዳንድ ትንሽ ገንዘብ ለሚድረግ የቻሉ ወጣቶችም ቢሆኑ አከባቢውን እየለቀቁ በትልልቅ ከተሞች በማስፈር ላይ ናቸው። ስለሆነም በዚህ ፍልሰት የተነሳ በተለይ በዓዲግራት ከተማ አንድ ቀበሌ የአርብ ቀበሌ የሚል ማጠሪያ እስከማግኘት ደርሷል። የነዚህ ሽማግሌዎችና ዕድሉን ያገኙ የአርብ ብሄረሰብ አባላት አከባቢውን እየለቀቁ መፍለስ እንደ አርብ በማለ አናሳ ብሄረሰብ ባህሉን፣ ቋንቋውንና ታሪኩን ጠብቆ መቀጠል ላይ ለወደፊቱ ሊኖረው የምችለው አሉታዊ ተጽእኖ ለማመት ምንም ከባድ አይደለም። ከሚኖሩት አሉታዊ ተጽዕኖዎች አንዱን ለመጥቀስ ያህል፣ በነዚህ ሽማግሌዎች ወደ ትልልቅ ከቶሞች ፍልሰት ምክንያት ባህሉን ታሪኩን ወደ ቀጣዩ ትወልድ በአከባቢው ሊያስተላልፉልን የሚቹሉ ሰዎች በቦታው እያጣን ነው፣ በሌላ ቋንቋና ባህል ወስጥ የሚወለዱና የሚያድጉ ልጆች ባህላቸውንና ቋንቋቸውን ትተው ሌላ ቋንቋና ባህል ይዘው እንዲያድጉም እየተደረገ ነው።

## 6. <u>የሻዕቢያ ወረራ ያስከተለው የህይወት፣ የንብረት ወድመትና የተወሰነ መሬት ለኤርትራ ማስጠት</u>

በ1990 ዓ.ም የኤርትራ መንግስት የኢትዮድያ ሉዓላዊ ግዛቶችን ለሚጀሚያ ጊዜ ሲወር ያለ ምንም ወታደራዊ ሀይል በአከባቢው ሳይኖር ከወረራቸው አከባቢዎች የአርብ ወረዳም እንዷ ነበረች። ቀየው ሲወረር የአርብ ህዝብ ሜሬቱን አላስነካም በማለት ከትልቅ እስከ ትንሽ በአንድነት በመነሳት እስከ አፍንጫው የታጠቀውን የሻዕቢያን ወራሪ ሰራዊት ለብቻው ካለምን የመንግስት እርዳታ ለቀናቶች ተጋፍጦ በርካታ የአርብ ልጆች ወድ ህይወታቸውን ለዳር ድንበራቸው እንደከፈሉ የሚታወቅ ሀቅ ነው። የአርብ ህዝብ ሻዕቢያን ባገኘው መሳሪያ ለቀናቶች ለመጋፈጥ ቢሞክርም የኢትዮድያ ሰራዊት በወቅቱ ሊደርስለት ሰላልቻለ ሻዕቢያ ሊቆጣጠራው የፈለገውን የአርብ ሜሬት በሙሉ ተቆጣጥሮ፣ መዝረፍ የምችለውን ንብረት በሙሉ ዘርፎ፣ በተቆጣጠረው አከባቢ የነበረውን ህዝብ እንዳለ ምርኮኛ አድርጎ ለተወሰነ ጊዜ እንደ ምርኮኛ ወስዶ እንደነበረ ሁላችን የምናወቀው ነው።

ሌላው በ1990 ዓ.ም. የሻዕቢያ ወረራ ወቅት በሻዕቢያ ከተፈጸመት አሳዛኝና አሰብአዊ ድርጊቶች ወስጥ ከ100 በላይ የሚሆኑ ንጹሃን የአርብ አርሶ አደሮች ጠልፎ መወሰድ ነው። የነዚህ በ1990 በሻዕቢያ የተጠለፉ ንጹሃን አርሶ አደሮች መዳረሻ አይተወቅም፣ ተገድለው ይሁን በህይወት ይኑሩ እስከዛሬ ምንም የሚታወቅ ነገር የለም። የኢትዮድያ መንግስት ሆነ የሚማለከታቸው ለሰው ልጅ ሰብአዊ መበት ተሟጋች ድርጅቶች ሻዕቢያ የነዚህ አርሶ አደሮች መዳረሻና ሁኔታ እንዲያሳወቅ ያደረጉት ጥረት የለም። በመሆኑም የአርብ ህዝብ በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ የነዚህ ደብዛቸው የጠፉ ወገኖች የቅርብ ቤተሰቦቻቸው እስከ ዛሬ ድረስ ቁርጠኑ ሳያወቁ የሀዘን ማቅ እንደለበሱ ይገኛሉ።

ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነውና የሚያበሳጨው ደግሞ ያ ሁሉ ህይወት የተከፈለበት፣ ብዙ ንብረት የወደማበት፣ አንድም ቀን በኤርትያ አካልነት የሚታወቀው የአሮብ ህዝብ የሚኖርበት የኢትዮጵያ መሬት በኢትዮጵያ መንግስት የሄግ ወሳኔ እየተባለ በሚታወቀው የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛቶች ለሻዕቢያ በስጦታ የተሰጠበት ወሳኔ ማስረት ለሻዕቢያ ማስጠቱ ነው። በትክክል የተኛው የአሮብ መሬት ነው ለሻዕቢያ የተሰጠው የሚሰወን ለማወቅ የሚፈልግ የሄጉ ወሳኔንና በዚህ ወሳኔ ማስረት ድንበር እንዲያካልል የተቋቋመው የደንበር አካላይ ኮሚሽን የድንበር ካርታ መመልከት ነው።

## 7. <u>በአከባቢው ድንበር ጥበቃ በሚል የሰፈረው ሰራዊት ያስከተለው የትዳርና ኑሮ መፋለስ</u>

በትክክል ሰራዊቱ ሰፍሮበት ያለወን ማንደሮች ለይቼ ባላወቅም ባሁኑ ጊዜ በበርካታዎቹ የአድጋዲዓና በክናይቲዓረ ማንደሮች የኢትዮጵያ ሰራዊት ሰፍሮ እንዳለ የሚታወቅ ነው። በርግጥ ዳር ድንበር ማጠበቅ ካለበት ሰራዊት በድንበር ላይ ማስፈር የነበረ፣ መኖር ያለበትም ነው። የጦር ሰራዊት ከህዝብ ጋር ተደባልቆ፣ የአርሶ አደሮችን ቤት መኖሪያው አድርጎ መቀመጥና መኖር ግን አነጋጋሪና አጠያያቂ ነው።

ስለ ችግሩ ስፋትና ጥልቀት በዝርዝር ለመናገር ቢከብደኝም፡ ለድንበር ጥበቃ በሚል የኢትዮጵያ ሰራዊት በሰፈረባቸው ማንደሮች የሚኖሩ የአንዳንድ አርሶ አደሮች ትዳርና ኑሮ እየተፋለሰና እየተወሳሰበ መሆኑን ግን እርግጥ ነው። አንዳንድ ወጣት አርሶ አደር ሴቶች በተለያየ ጥቅማጥሞች እየተታለሉ፣ አንዳንዷም እየተገደዱ በትዳራቸው ላይ ከወታደሮቹ ጋር እያማገጡ መሆናቸውና ይህም ለትዳሮች መፍረስ ምክንያት እየሆነ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ብቻ አይደለም አንዳንድ ወታደሮች በሚያሳዩዋቸው ከሞራል ውጭ የሆኑ ከእንስሳ ጋር የሚፈጸም ወሲብ ህጻናትና ወጣቶች እየተማለከቱት በሚያግ ላይ ናቸው። አንዳንድ ወጣቶችም አንዳንድ ወታደሮች በሚያደርጉት ወጣት ህቶቻቸው ወይም ጓደኞቻቸው ለግብረስጋ ስጋ ግኑኝነት ሚፈለግ ድርጊት አላስችል ብሎዋቸው ከወታደሮቹ ጋር በማጋጨት እየታሰሩና እየተደበደቡም ነው።

## 8. <u>መደምደሚያ</u>

በመጣጥፌ ከላይ እንደገለጽኩት የአሮብ ብሄረሰብ አባላት በሀገር ወስጥ ያለወን በትክክል ባላወቅም በውጭ በተለይ በአሜካ፣ በአወሮፓ፣ ወዘተ. የመናገርና የመጻፍ ነጻነት ባለበት ዓለም የምንኖር የአሮብ ተወላጆች በሀገርቤት ያለው ህዝባችን ያለበት ችግር ግጅፈትና ወስብስብነት ላይ በጣም የተለያየ አማካከት እንዳለን ግልጽ ነው። ይህን ልዩነት ለማጥበብ ብሎም ወደ አንድነት ለማማጣት የግልጽ ወይይት አስፈላጊነት ስለታየኝ በኔ እይታና እምነት የአሮብ አናሳ ብሄረሰብ እንደ ብሄረሰብ የመቀጠል ዕድሉን አደጋ ወስጥ ያሰገቡ ናቸው ያልኩዋቸወን ችግሮች አጠር አጠር በሚደረግ ከላይ ለማስቀመጥ ሞክሪያለሁ።

በመጣጥፌ ወሰጥ ከላይ እንዳስቀመጥኩት የመንግስት ደጋፊ ነን የሚሉ ወገኖች ከተፈጥሮ አመጣሽ ችግሮች ውጭ ዛሬ የአሮብ ህዝብ ሌላ ችግሮቹ በኢህአዴግ መንግስት ተቀርፈወለታል ባዮች ናቸው። እኔ ግን ከተፈጥሮአዊ ችግሮች ይበልጥ ዛሬ የአሮብ አናሳ ብሄረሰብን ህልውና እየተፈታተኑ ያሉ ችግሮች ከምንጊዜም በላይ ገዝፈውና ገሃድ ወጥተው የሚገኙት ዛሬ በኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን በክልሉ በስልጣን ላይ ባለው ፓርቲ (በህወሓት) እየተፈጸሙ ያሉ ድርጊቶች ናቸው ባይ ነኝ።

እንደኔ እምነት ሌላው ማስረታዊ ችግራችን ደግሞ በግምትና በስሜት ከማዳት ያለፈ በትክክለኛ ጥናትና ሚጃ ላይ የተማሰረተ ስለ ብሄረሰባችን ዛሬ ያለበት ተጨባጭ ሁኔታ እወቀት የሌለን መሆናችን ነው።ስለሆነም ባለሞያዎች ይህን ጥናት ለሚድረግና ለማቅረብ ተነሱ እላለሁ። ሌላም ወገኖቼ የአሮብ ልጆች እስካሁን እየተደማመጥን አይደለንምና ቢያንስ ለመደማመጥ እንሞክር። አሁን ገብተንበት ካለነው መጥፎ የጥላቻና የእልህ ባህል ወጥተን ህዝባችን አሁን ካለበት ሁለንተናዊ ችግር ለማላቀቅ በጋራ እንነሳ። ጊዜው በጣም የዘገየ ቢሆንም አሁንም ምንም ካለሚድረግ ዘግይቶ ቢሆንም መጀመር የግድ አስፈላጊ ስለሆነ የአሮብ ህዝብ ጉዳይ ያገባናል፣ ይማለከተናል የምንል የብሄረሰቡ ተወላጆች ሁሉ በጉዳዩ ላይ በግልጽ መወያየት መቻል አለብን። ስለሆነም በአካል ለማናኘት የምንችል በአካል በማናኘት፣ በአካል ለማናኘት የማንችል ደግሞ ዘመኑ የፈጠረልን ተክኖሎጂ በማጠቀም በግልጽ በጨዋ ቋንቋ መወያየትና የጋራ መፍትሄ ፍለጋ እንጀምር እያልኩ የዛሬ መጣጥፌን አበቃለሁ።